# ኢሕአዴግ የሚወገድ እንጂ የሚጠገን ስርዓት አይደለም!

ሰሞኑን የአሜሪካ ዋና ከተማ ዋሽንግተን የኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ሆና ከርማለች።አገሪቱን ለሃያ አምስት ዓመት ቀስፎ ፣ሲበዘብዝ፣ሲገልና ያገሪቱን ድንበርና አንጡራ ሃብት ከውጭ ሃይሎች ጋር ሲቀራመት የቆየው ወያኔ መራሹ ኢሕአዴግ በሕዝብ ተቃውሞ ማእበል ከተጥለቀለቀ ወራቶች አልፈዋል፡በኦሮሞው፣በጋምቤላው፣በኦጋዴው፣በቤኒሻንጉል፣በጋምቤላ ተወላጅ ብቅ እልም እያለ ሲካሄድ የቆየው ትግል ከሳምንታት በፊት ለዓመታት ሲብላላ የቆየው የአማራው ኢትዮጵያዊነትን የተላበሰ የሕዝብ ቁጣና የለውጥ ፍለጋ አመጽ ከዳር እከዳር እየተቀጣጠለ በመሄድ ላይ በመሆኑ ወያኔንና ደጋፊዎቹን ሽብር ላይ ጥሏቸዋል።ይህን ሕዝባዊ አመጽ ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ማንም የፖለቲካም ሆነ የታጠቀ ድርጅት ሳይገባበትና ሳይመራው ሕዝቡ እራሱ በወሰደው ቆራጥነት የተካሄደ የነጻነት ትግል መሆኑ ነው። ሳይከፋፈል በአንድ ዓላማ ቆሞ ሊቀጥል የቻለውም ለሥልጣን ሳይሆን ለነጻነት የሚደረግ ሕዝባዊ ትግል በመሆኑ ነው።

የወያኔ መሪዎች  አባይ ጸሃየ፣ሳሞራ የኑስና የመሳሰሉት ወንጀለኞች ስጋት ሲወጥራቸው ከቀናት በፊት ሥልጣን ላይ ያወጣቸውን የአሜሪካንን መንግሥት ለመማጸን ዋሽንግተን ገብተው እንደተማከሩና፣እኛ ከሌለን አገሪቱ ብጥብጥ ውስጥ ትገባለች፣ከባቢውም በኢሲስ አሸባሪ ሃይል ይጥለቀለቃል የሚል ተረትተረት ይዘው መቅረባቸው ታውቋል።በጣም የሚገርመው አልሸባብን እንዳይጠፋ ስውር ድጋፍ እያደረገ ጸረ ሽብር ነኝ ብሎ ዓለምን በማሞኘት እርዳታ በመሰብሰብ የተካነው ወያኔ መራሹ ቡድን ፣አልሸባብና ሽብር የገቢ ምንጬ አድርጎ ስለሚጠቀምባቸው እንዲጠፉ አይፈልግም።እነሱ ጠፉ ማለት የገቢ ምንጬ ደረቀ ማለት ነው።ከምዕራቡ ከሚያገኘው ድጋፍና እርዳታ በተጨማሪ መሣሪያ የሚሸጥለት ደንበኛው በመሆኑ አልሸባብን ደፍሮ ከልቡ አይዋጋውም።እንደማስፈራሪያ ይጠቀምበታል። አሜሪካኖቹም ቢሆኑ ከልባቸው የሽብር ሰንሰለቱ እንዲበጠስ አይፈልጉም፤ምክንያቱም በዚያ ሰበብ የመከላከያ ተቋማቸውን ለመገንባትና መሣሪያም ለመሸጥ ስለሚረዳቸው ነው። የሚተማመኑበት ወያኔ መራሹ ኢሕአዴግ ሥልጣኑን እንዲያጣ አይፈልጉም።ወያኔ ተወገደ ማለት በአፍሪካ ደረጃ ለዘረጉት የዘረፋ መረብ ተባባሪና አጋር ማጣት ማለት ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል መሳካት በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገኙት የአፍሪካና የሌላ አገር ሕዝቦች ለሚያደርጉት የለውጥ ትግል ምሳሌ ስለሚሆን በተፈለገው መንገድ ማዳፈኑን ይመርጣሉ።ግፋ ቢል በጥቃቅን ጥገና የሚፈልጉት ስርዓት እንዲቀጥል ለማድረግ ይሞክራሉ።በኢትዮጵያም የሕዝቡን ትግል ለመቀልበስና  ከነጭራሹም ለማጥፋት ጥቃቅን ጥገና እንዲደረግ ፍላጎት እንዳላቸው መግለጻቸው ታውቋል።በሌላም በኩል በአገር ቤት ከሚገኙት የተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል በህይወት የቆዩት(ለምን እንደቆዩም የሚታወቅ ባይኖርም ለስርዓቱ ካላቸው የተለሳለሰ አቋም ሊሆን ይችላል የሚል አስተሳሰብ በሰፊው ይወራል)የመድረክ ም/ሊቀመንበር ዶር.መረራ ጉዲናና የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር እንጂነር ይልቃል ጌትነት ሰሞኑን፣እስከአሁንም ድረስ በዚችው የአሜሪካ ዋና ከተማ ሲንቀሳቀሱ የከረሙ ሲሆን በአሜሪካም መንግሥት አስተዳርና የውጭ ጉዳይ ቢሮ በተደረገላቸው ጥሪና ግብዣ በአገሪቱ አሳሳቢ ጉዳይ ላይ እንደተወያዩ የሚገልጽ ሾልኮ የወጣው መረጃ ሲያረጋግጥ ሁለቱም ሳይክዱ ይፋ አድርገዋል።መረጃውና የየድርጅቱ መሪዎች እንዳስረዱት የአሜሪካ መንግሥት የጥገና ለውጥ ተደርጎ ያለው ስርዓት እንዲቀጥልለትና እነሱም እንዲተባበሩ የተጠየቁ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው።

በአገርቤትም ይኸው ጉደኛ  የአገዛዙ ቡድን አከርካሪቱን ሰብሬዋለሁ ብሎ የፎከረበትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን መሪ አድርጎ በሾመው ጳጳስ በኩል ሕዝቡ በተለይም ወጣቱ ትግሉን እንዲያቆም ወላጆች ተጽእኖ እንዲያደርጉ ና ቀሳውስትም ታቦት ተሸክመው ሕዝቡ እንደታቦቱ ወያኔን ተሸክሞ እንዲኖር ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኙ ታውቋል።ሕዝብ በገፍ ሲገደል፣ ሲታሰር፣ሲሰደድ፣ሲቆስል ድምጹን ያላሰማና የፈጣሪን ትዕዛዝ ጥሰሃል ብሎ መንግሥትን ያልጠየቀ ጳጳስ አሁን ከወንጀለኞቹ ጎን ቆሞ ለነጻነት የሚደረገውን ትግል ለማኮላሸት መሞከሩ  የውጭ ወራሪዎችን የተከላከለችውን አገር ወዳድና አርበኛ የሆነችውን ቤተክርስቲያኗን

ማርከስ ይሆናል።ቤተክርስቲያኗ ሊያጠፋት ለተነሳው አገር በቀል ጠላት መሳሪያ ሆና እጇን በእጇ እንዳታጠፋ ቀሳውስቱ የተዘረጋውን ሴራ ተገንዝበው ማውገዝና ከሕዝቡ ጎን መሰለፍ አለባቸው።መማጸን ያለባቸው የተበታተነው ሕዝባዊ ሃይልና የተቃዋሚው ጎራ እንዲሰባሰብና በአንድነት እንዲቆም በማድረጉ ተግባር ላይ መሆን ይኖርበታል።

በሌላው ዙሪያ ባለፈው ሰኞ ኦገስት 8 ቀን 2016 ዓ.ም. በዋሽንግተን ከተማ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከመቸውም ጊዜ በበለጠና በደመቀ ሁኔታ ብዙ ሰው የተሳተፈበት ሰላማዊ ሰልፍ አድርገው የአሜሪካ መንግሥት ለወያኔ መራሹ አስተዳደር የሚያደርገውን እርዳታ እንዲያቆም፣ በተጨማሪም በሰላማዊ ሕዝብ ላይ የግድያና ወንጀል የሚፈጽመው ቡድን በሕግ እንዲጠየቅ፣ሕዝቡ የመረጠው አስተዳደር እንዲመሰረት ጠይቀዋል።ይህም ቢሆን ለአሜሪካን መንግሥት ሌላ እራስ ምታት ነው።ተቃውሞውን ባይወዱትም በገዛ ቤታቸው ደጃፍ ሲመጣ በዝምታ ሊያልፉት አይችሉም።ግን ስር ነቀል መፍትሔ እንዲመጣ ይፈልጋሉ ማለት አይደለም።

አሜሪካኖች የሚያካሂዱት ሙከራ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ሙሉ መልስ የሚሰጥ ሳይሆን የአገዛዙን ሕገመንግሥት ተቀብሎ እንዲያድር የሚያስገድድ ሁኔታ ለመፍጠር እንደታሰበ የሚያረጋግጥ ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ከበስተጀርባው ለሚጎነጎን ሴራ ትኩረት ሳይሰጥ በጀመረው የነጻነት ትግል እንዲቀጥልበት ማሳሰብ ይገባል።ሰላምና ድርድር አስፈላጊ መሆኑ ቢታመንም የብዙ ወጣቶችና ዜጎች ሕይወት የጠፋበት ትግል ተቀልብሶ ወንጀለኞች በሕግ ሳይጠየቁ በመንበራቸው ላይ እንዲቆዩ የሚደረገውን የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ጥረት በውስጥና በውጭ የሚታገለው ኢትዮጵያዊ ማውገዝና መከላከል ይኖርበታል።ያ ካልሆነ ግን ውጤቱ እንዳለፉት ጊዜያቶች ወጣቱን አሳልፎ በመስጠት መስዋእት አድርጎ ባዶ እጅ መመለስ ይሆናል።የትግሉ ዓላማ የጥገና ለውጥ ማድረግና ወንጀለኛው ቡድን በስልጣን ላይ እንዲቆይ ማድረግ ሳይሆን አማራጩ መንገድ በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ተወግዶ በምትኩ ሁሉንም ያሳተፈ የሽግግር መንግሥት መመሥረት ብቻ ነው።ያ እስኪሆን ድረስ ሕዝቡ ትግሉን መቀጠል ይኖርበታል፤በተስፋ ተደልሎ ለዳግማዊ የበቀል እርምጃና ጥፋት በር መክፈት አይኖርበትም ።የ97ቱን ተመክሮ ሊያስታውሰው ይገባል።

የተቃዋሚ ሃይሎች የሕዝቡን ፍላጎትና ጥያቄ ከግቡ ለማድረስ ተባብረው ከጎኑ መሰለፍ እንደሚገባቸው ሊያውቁት ይገባል፤ከሕዝብ ጀርባ በማንኛውም ሃይልና አገር ግፊትና ሽንገላ የጥገና ለውጥ እንዲመጣ መተባበርና ሃሳቡን መቀበል የወንጀለኞች ስርዓት እንዲቀጥልም መፍቀድ ከጥፋት ሃይሎች ጎን እንደሚያሰልፋቸው በቅድሚያ ሊገነዘቡት ይገባል።የሕዝቡን ጥያቄ በማክበር ከጎኑ ሲቆሙ ብቻ ነው ሕዝባዊና አገር ወዳድነታቸው የሚረጋገጠው።በውጭ ሃይል ከመተማመን በራስ ሕዝብ መተማመኑ ማዋጣት ብቻ ሳይሆን ያኮራል።ወያኔንና አሜሪካኖችን አሳብ ላይ የጣላቸውና ለጥገና ለውጥ የገፋፋቸው የሕዝቡ ትግል መፋፋም ነው፤ይበልጥ ሲፋፋም ደግሞ ለከፍተኛ የሕዝብ ጥያቄ ማለትም ለሽግግር መንግሥት መመስረት ጥያቄ ማጎብደዳቸው አይቀርም።

በሕዝቡ ትግል ላይ ውሃ ለማፍሰስ የሚሞክሩ እንዳሉ ሁሉ ትግሉንም ለማቀናጀትና ከግቡ ለማድረስ የሚጥሩ ሕዝባዊ ሃይሎች በየአቅጣጫው በመፈጠር ላይ ናቸው።እነዚህ የለውጥ ሕዝባዊ ሃይሎች ተጠናክረውና ተቀናጅተው ለድል እንዲበቁ ማድረግ የአገር ወዳዱ ድርሻ ነው።በየወረዳው ሕዝባዊ ሃይሉ አስተዳደሩን ከጨቋኞች መዳፍ ነጻ ቢያወጣ ለዘለቄታው የሽግግር መንግሥት ምስረታ ሂደት የመጀመሪያው እርምጃ ይሆናል።ይህ ድል እንዳይከስም የሚያስፈልገው ድጋፍ መቅረብ ይኖርበታል።አገዛዙ ለመኖር ሲል የማያደርገው ሙከራ አይኖርም።ሁሉም ሙከራ ካልሰራለት በመጨረሻው አስተዳደሩን ወታደራዊው ሃይሉ እንዲቈጣጠረውና የማምለጫ በር እንዲከፈትለት እንደሚያደርግ በኦሮሞና በደቡብ ክልሎች የታየው ሂደት ማስረጃ ነው።አሜሪካኖቹም ቢሆኑ ወያኔ ተዳክሞ ሕዝባዊው ትግል የበላይነቱን ከያዘ እንደ ግብጽ የወታደር መንግሥት በሾኬ ሥልጣኑን ይዞ ጥቅማቸውን ቢያስከብርላቸው ይመርጣሉ።

በውጭ አገር ያለው ለውጥ ፈላጊ ኢትዮጵያዊ ክልል፣ቋንቋ፣ እምነትና ድርጅታዊ አቋም ሳያግደው እጅ ለእጅ ተያይዞ ለአገር አድኑ ትግል የሚያስፈልገውን ድጋፍ ማበርከት

ይጠበቅበታል።የሚከተሉትን ተግባራት ለማሟላት ከቻለ የውስጡ ትግል ተጠናክሮ ለድል እንደሚበቃ አያጠራጥርም።ምንም ጊዜ ቢሆን የሕዝቡን ትግል አሳልፎ ለሚሰጥ ውልና ድርድር ሳያጎበድድ ብዙ ወጣቶችና አገር ወዳዶች መስዋእት የሆኑበት ትግል ከዳር እስኪደርስ መፋለም አለበት።የተጀመረው ሕዝባዊ ትግል እንዲጠናከርና ግብ እንዲመታ የሚከተሉትን እርምጃዎች መወሰድ ይኖርበታል።

1. ኢትዮጵያዊ በያለበት አገር ለመንግሥትና ለሰብአዊ መብት ድርጅቶች ሁኔታውን በማስረዳት በገዢው ቡድን ላይ የኤኮኖሚና የዲፕሎማቲክ ተጽእኖ እንዲያደርጉ፣ለሕዝቡ መብት ጥያቄ እንዲተባበሩ መጠየቅ።ቢቻል በአንድ ቀን በተመሳሳይ መፈክር ዙሪያ ዓለም አቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ ዝግጅት ማድረግ።ለበቂ ዝግጅትና እንዲሁም ከሚኖረው ስነልቦናዊ እድምታ መጭው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት መስከረም 1 ቀን 2009 ዓ.ም.(September 11) ለዚህ የጋራ ትግል ዕለት ቢሆንና ዝግጅቱ ከአሁኑ ቢጀመር።ይህ ማለት ግን እስከዚያ ድረስ ዝምታ ይስፈን ማለት አይደለም።ትግሉን ማንጸባረቅና ማስተጋባት ይቁም ማለት አይደለም።በተገኘው አጋጣሚና ቀዳዳ መቀጠል አለበት።የተከፈተውን የነጻነት መስኮት ሳይዘጋ በር እንዲሆን ማድረግ ይገባል።

2. ለሚታገለው ሕዝብ የአቅም ግንባታ ማለትም፣ለተፈናቀለው መቋቋሚያ ፣ለሚታገለው ለስንቅና መጓጓዣ፣የግንኙነቱን መስመር ለማዳበርና ትግሉን ለማያያዝ በሚረዳው ተግባር ላይ የሚውል የገንዘብ እርዳታ ማሰባሰብ፣በየቤተክርስቲያኑ፣በየሬስቶራንቱና በሱቅና የንግድ ተቋም የገንዘብ መሰብሰቢያ ሳጥን በማስቀመጥ እርዳታ መሰብሰብ።ይህን ተግባራዊ የሚያደርግ በየአገሩ ከሁሉም የተውጣጣና ታማኝነት ያለው ግብረሃይል ማቋቋም።በየአቅጣጫው የሚሰበሰበው ገንዘብ በአንድ የባንክ ቁጥር እንዲገባ ማድረግ።ወደተፈለገው ቦታና ተግባር እንዲደርስ የሚቻልበትን መንገድ ማጥናትና ተግባራዊ ማድረግ።

3. ለቆሰለው የሕክምና እርዳታና መድሃኒት በአስቸኳይ ለማሟላት ጥናትና ዝግጅት፣አገር ውስጥ ያሉት የሕክምና ባለሙያዎችም ከሕዝቡ ጎን ቆመው በሙያቸው እንዲተባበሩ ማድረግ።

4. በወያኔ/ኢሕአዴግ የተፈጸመውን ወንጀል፣ግድያና ማቁሰል፣አስመልክቶ መረጃ ማሰባሰብ፣ በሕግ የሚጠይቅ አካል ለመፍጠር በሙያው የተሰለፉ ኢትዮጵያውያን ተገናኝተው በአገር ውስጥና ለዓለም ፍርድ ቤት የሚቀርብ ክስ ለመመስረት ዝግጅት እንዲያደርጉ ጥሪ ማድረግ።ይህ አንዱ የትግል አካል እንደሆነም ማሳሰብ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!!

አገሬ አዲስ